www.chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲፫
አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No 13
ADDIS ABABA 17th February, 2021

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፬፻፹፫/፪ሺ፲፫

የዕዳ እና የሀብት አስተዳደር ኮርፖሬሽን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.....ገጽ ፲፪ሺ፱፻፸፰

Content

Regulation No.483 /2021

Council of Ministers Regulations to provide for the Establishment of Liability and Asset Manangement Corporation.....page 12978

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፹፫/፪ሺ፲፫

የዕዳ እና የሀብት አስተዳደር ኮርፖሬሽን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፺፻፶፯/፪ሺ፲ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የዕዳ እና የሀብት አስተዳደር ኮርፖሬሽንን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፹፫/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

Council of Ministers Regulation No. 483/2021

COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF LIABILITY AND ASSET MANANGEMENT CORPORATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 1097/2018 and Article 47 (1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

PART ONE
GENERAL

1. Short Title

This Regulation may be cited as "Liability and Asset Management Corporation Establishment Council of Ministers Regulations No.483/2021."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

www.chilot.me

፪. መቋቋም

ሀ/ የዕዳ እና የሀብት አስተዳደር ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

ለ/ ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፺፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡ ፡

፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የገንዘብ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

፬. ዋና መሥሪያ ቤት

የ ኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ስፍራ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

፭. ዓላማ

ኮርፖሬሽኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ ከገንዘብ ሚኒስቴር በሚደርሰው ዝርዝር መሰረት የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ዕዳ ይረከባል፣ ከኢንዱስትሪ ልማት ፈንድ የሚመደብለትን ካፒታል፣ ከንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚያገኘውን ገቢ፣ እንዲሁም ከሌሎች ምንጮች የሚመደብለትን ገንዘብ በመጠቀም ይህንኑ ዕዳ ይከፍላል፣

፪/ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወደ ግል የሚተላለፉ እንዲሁም የሚፈርሱ የመንግስት ልማት ድርጅቶችን ንብረት እና ዕዳ በመረከብ ያጣራል እና ያስተዳድራል ፣

፫/ ከመንግሥት የሚመደበው ካፒታል እና ሌሎች ገቢዎች ለዕዳው ክፍያ እስከሚውል ድረስ አዋጭነታቸው በተረጋገጠ የኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

2. Establishment

a/ There hereby is established Liability and Asset Management Corporation (hereinafter the "Corporation") as a public enterprise.

b/ The Corporation shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. Supervising Authority

The Ministry of Finance shall be the supervising authority of the Corporation.

4. Head Office

The Corporation shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. Objective

The objectives of the Corporation are the following:

1/ Takeover the liabilities of public enterprises as per the list it receives from the Ministry of Finance and service such debt using capital to be allocated from the Industrial Development Fund, revenue generated from its business activities and other resources that may become available to it;

2/ Takeover the residual assets and liabilities of public enterprises that are being partially or whole privatized or the liquidation of public enterprises upon their dissolution;

3/ Invest the capital injected by the Government for debt service payment of public enterprises and other resources until it is used for repayment of such loan;

www.chilot.me

፬/ ለአበዳሪ ተቋማት የዕዳ ማሰባሰብ እና ማስተዳደር አገልግሎት ይሰጣል፣

፭/ ከመንግሥት የሚረከበውን የሕዝብ ሀብት ያስተዳድራል፣

፮/ ጥቅም ላይ ያልዋሉ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ንብረቶችን ገቢ በሚያመነጭ ሥራ ላይ ያውላል፣

፯/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ተግባራትን ያከናውናል።

፮. ካፒታል

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደለት ካፒታል ብር ፭፻፸ቢ (አምስት መቶ ሰባ ቢሊዮን ብር) ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር ፩፻፵፪ ቢሊዮን (አንድ መቶ አርባ ሁለት ቢሊዮን ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል።

፯. ኃላፊነት

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

፰. ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም

ዓብይ አህመድ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

4/ Render debt collection and management services to other creditors;

5/ Takeover and manage public assets that may be assigned to it by the Government;

6/ Transform property of public enterprises that are not put in use into income generating ventures;

7/ Engage in other related activities necessary for the attainment of its objectives.

6. Capital

The authorized capital of the Corporation is Birr 570,000,000,000 (five hundred seventy billion) of which Birr 142,000,000,000,000 (one hundred forty two billion Birr) is paid-up in cash and in kind.

7. Liability

The Corporation shall not be liable beyond its total assets.

8. Duration

The Corporation is established for an indefinite duration.

9. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Abeba, On this 17th Day of February, 2021.

ABIY AHMED (DR.)
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA